Australian Government
Department of Immigration and Border Protection

# ለተጠቃሚ መመሪያ

ፈቃድ ያለው የተመዘገበ ማይግሬሽን/መጤ ወኪሎች ለሙያ ብቃት የሚያሟሉ ባለሙያዎች እንደሆኑና በስነ-ምግባር ደንብ የሚከተሉና በወቅታዊ ማይግሬሽን ህግና አሰራር ሂደት መሰረት ለመከተል እውቀት ያላቸው ሰዎች ናቸው።

የርስዎ ተወካይ በOMARA (Office of the Migration Agents Registration Authority) መመዝገብ እንዳለበት፤ ይህም ለኢሚግሬሽን አገልግሎት መስጠት የሚችል ለዚህ ብቁና ተስማሚ የሆነ ሰው መሆን እንዳለበት ነው። ተወካዩ ስለመመዝገቡ ለማጣራት የ OMARA በድረገጽ: www.mara.gov.au ላይ ማየት።

## የማይግሬሽን ተወካዮችና ስነ-ምግባር

በስነ-ምግባር ደንብ የሚረጋገጠው ስለሚከተለው በርስዎ የተመዘገበ ማይግሬሽን ተወካይ በኩል መካሄዱን ማረጋገጥ:

- እርስዎ ቪዛ ስለማግኘት እድል መረጋገጥ ሓቀኛ መሆን;
- ስለ ማመልከቻዎ እድገትና በዚህ ላይ ተጽእኖ ስለሚያሳድር ማንኛውም ለውጥ ለርስዎ ማሳወቅ ;
- በሥራ ሰዓታት ማነጋገር እና አድራሻቸውን ከቀየሩ ለርስዎ መናገር;
- የርስዎን ፍላጎት በጥሩ ለማሟላትና የርስዎን ግላዊ መረጃ ለመከላከል በህጉ መሰረት መሥራት;
- በርስዎ ማመልከቻ ላይ ችግር ሊፈጥር የሚችል የሆነ ፍላጎት ካለ ማሳወቅ እና ከፍላጎትዎ ጋር ግጭት ከፈጠረ አለመቀበል ;
- ሥራው ከመጀመሩ በፊት — ጽሁፋዊ መግለጫ ለርስዎ ማቅረብ — ስለሚቀርበው አገልግሎት፣ የዋጋ ግምትና ለሌሎች ወጪዎች ማሳወቅ;
- ተገቢ የሆነ ክፍያ ማስከፈል እና በቅድሚያ የሚከፍሉ ከሆነ ይህንን በተለየ ባንክ አካውንት ማስቀመጥ;
- ለተጠናቀቀ አገልግሎቶች ዝርዝር የመክፈያ ወረቀት እና መከፈል ያለበት የገንዘብ መጠን የሚገልጽ ማቅረብ;
- ትክክለኛ የሆነ ምክር በወቅቱ ማቅረብና በተቻለ ፍጥነት ስለማመልከቻዎ ውጤት በጽሁፍ አድርጎ መናገር።

## ቅሬታ

ከተመዘገበ ማይግሬሽን ተወካይዎ ጋር ችግር ካጋጠምዎት መፍትሄ ለማግኘት ከነሱ ጋር መሞከር አለብዎ። እርዳታ ለማግኘት OMARA ማነጋገር።

*ለ OMARA ቅሬታ ማቅረብ በርስዎ የቪዛ ማመልከቻ ላይ ችግር አይፈጥርም።*

## Office of the Migration Agents Registration Authority (OMARA)

በአውስትራሊያ ህግ መሰረት፣, OMARA:

- የማይግሬሽን ተወካይ ለመሆን ምዝገባ ማመልከቻ ማጥናትና ስለመወሰን;
- ተወካዮች የሙያ ችሎታ እንቅስቃሴዎችን በቀጣይነት ማሻሻል;
- ለተመዘገበ የማይግሬሽን ተወካዮች የሥራ ምግባራቸውን መከታተል; እና
- በተመዘገበ የማይግሬሽን ተወካዮች ላይ የሚቀርብን ቅሬታ/ክስ ማጣራትና ተገቢ ከሆነም ሥርዓት እንዲይዙ ማድረግ።

ከርስዎ ቪዛ ወይም ከስፖንሰር ድጋፍ ማድረግ ወይም ለርስዎ ማይግሬሽን ተወካይ የተከፈለን ክፍያ ለማስመለስ በተዛመደ OMARA እርዳታ መስጠት አይችልም።

የበለጠ መረጃ በድረገፅ www.mara.gov.au ላይ ማግኘት ይቻላል:

- ስነ-ምግባር
- ለተመዘገበ የማይግሬሽን ተወካይ ለመጠቀም ምክሮች
- ለተወካይ አማካይ ክፍያ

## አንድ ሰው ስለመመዝገቡ በድረገፅ www.mara.gov.au ላይ ማጣራት።

